| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "መነሻው ፡ ክዳት ፥ ... ፡ መድረሻው ፡ ጥፋት ። " |
| ደሁሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ግንቦት ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2016-004 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |



# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## መነሻው ፡ ክዳት ፥

## ... ፡ መድረሻው ፡ ጥፋት ።



ልክ ፡ የዛሬ ፡ 33 ፡ ዓመት ፥ ግንቦት ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ በተባበሩት ፡ የአሜሪኮ ፡ ኹነቶች ፡ (ተ.አ.ኹ / U.S.A.) ፡ መንግሥት ፥ የደርግን ፡ የውንብድና ፡ ይዘት ፡ እና ፡ ተቃዋሚዎቹን ፡ ተገንጣዮች ፡ ቡድኖች ፡ ሰብስቦ ፡ እና ፡ ለ"ዕርቅ" ፡ እሸመግላለኹ ፡ ባሎ ፡ ለዓለሙ ፡ ኹሉ ፡ በዋሸው ፡ መሠረት ፥ የዕርቅ ፡ ጉባኤ ፡ እብሪታንያ ፡ መዲና ፡ ለንድን ፡ ላይ ፡ ተቀጥሮ ፡ ነበር ።

ድንገት ፥ ገና ፡ ውይይቱ ፡ በቅጡ ፡ እንኳ ፡ ሳይዠመር ፥ የተባበሩት ፡ የአሜሪኮ ፡ ኹነቶች ፡ ተወካይ ፥ ጉባኤው ፡ እተቀጠረበት ፡ እ"በርቅ-ሸር ፡ ሆቴል" ፡ በራፍ ፡ አንድ ፡ አፍታ ፡ ወጣ ፡ ብለው ፥ ለተሰበሰቡት ፡ አወራኂዎች ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ዐጪር ፡ የክዳት ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ አስዘገቡ ፡—

***"የተ.አ.ኹ. ፡ መንግሥት ፡ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ኀይሎች ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማን ፡ ገብተው ፡ እንዲቈጣጠሩ ፡ ይጋብዛል ፤ ... ኤርትራም ፡ የራሷን ፡ ዕድል ፡ በራሷ ፡ እንድትወስን ፡ ይስማማል ፥ ውሳኔዋንም ፡ ይቀበላል ። "***

በዚህ ፡ ቃላቸው ፥ ባንዲት ፡ እግዝእት ፡ ሀገር ፡ የውስጥ ፡ ጉዳይ ፡ ጣልቃ ፡ መግባታቸውን ፡ እና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረትን ፡ መረምረማቸውን ፡ ባያጡትም ፥ በ"ኮምዩኒስቱ" ፡ ዓለም ፡ መኀርሰስ ፡ ማግስት ፥ የተ.አ.ኹ.ን ፡ ፈቃድ ፡ የሚገታ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ኀይል ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከንግዲህ ፡ አይኖረም ፡ ብለው ፡ ባመኑበት ፣ ታሪክም ፡ "ባከተመበት" ፣ የአንግሎ-ሳክሰኖች ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘላለማዊ ፡ ልዕልናም ፡ በታወጀበት ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ "ደርሰው" ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ አላስጨነቃቸውም ።

ሽምግልናው ፡ ማሞኛ ፡ ነበር ፤ በምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ ዘንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ዐልቋል ። ያች ፡ ለሺሕ ፡ ዓመታት ፡ አልሸነፍ ፡ ያለች ፡ ሀገር ፥ እንሆ ፡ ከ 80 ፡ ዓመታት ፡ ስርሰራ ፡ በኋላ ፥ ድንገት ፡ ወድቃ ፡ እና ፡ ደክማ ፡ ተገኘችላቸው ። ድል ፡ አደረግናት ፡ ለማለት ፡ ኹኔታው ፡ ባይፈቅድላቸውም ፥ የድል ፡ አድራጊነት ፡ ተከታታይ ፡ የበቀል ፡ ድርጊያዎቻቸውን ፡ በመልክተኞቻቸው ፡ አማካይነት ፥ እየተላላኩ ፡ እና ፡ እያስፈጸሙ ፥ እንዳቀዱት ፡ ኹሉ ፥ ኤርትራን ፡ አስገነጠሉ ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ንም ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ተኸሉ ፤ ብዙ ፡ ሌላም ፡ ጸያፍ ፡ እና ፡ የሚያስተዛዝብ ፡ ድርጊትን ፡ ፈጸሙ ።

እንሆ ፡ ከ 33 ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፥ ይህ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጥፋት ፡ ተወጥኖ ፡ የነበረ ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ቀድሞ ፡ መፈረካከስ ፡ ሲዠምር ፥ ኢትዮጵያ ፡ እንዳልሞተች ፡ ግልጽ ፡ ኾነ ፤ ኢትዮጵያ ፡ እንደማትሞት ፡ ለኛ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ የሚታመነውን ፡ ያኽል ፥ በእልክ ፡ ለተነሣሣው ፡ ለምልክዮሽ ፡ ኀይል ፡ አልቀጥለት ፡ ዐለ ። እልኩ ፡ ወደ ፡ ብስጭት ፡ ተለወጠ ። ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይዘነጣጥልልኛል ፡ ያለው ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፥ በድዱ ፡ የሚናከስ ፡ አሮጌ ፡ ኾብ ፡ ኾኖ ፡ ቈየው ፤ ሕጻናትንና ፡ ሴቶችን ፡ የሚያጉላላ ፣ የሚገድል ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ ፋኖ ፡ ያለ ፡ የታጠቀን ፡ ኀይል ፡ ገጥሞ ፡ የማይመክት ፡ ስኡን ፡ መኾኑን ፡ አገኘው ። ያ ፡ ኹሉ ፡ ምርምር ፣ ያ ፡ ኹሉ ፡ መራቀቅ ፣ ያ ፡ ኹሉ ፡ ዕቅድ ፣ ያ ፡ ኹሉ ፡ አፈጻጸም ፣ ያ ፡ ኹሉ ፡ "DV" ፣ ያ ፡ ኹሉ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

"USAID' ፣ … ፡ አንዱም ፡ የተጠበቀውን ፡ ክፉ ፡ ውጤት ፡ አሟልቶ ፡ አላስገኘለት ፤ **ኢትዮጵያ ፡ አለች ፥ አልሞተችም ።** ርግጥ ፡ ነው ፥ ባለፉት ፡ 33 ፡ ዓመታት ፥ በሚልዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ንጹሓን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሠቃቂ ፡ ኹኔታ ፡ በርሓብ ፣ በስደት ፣ በጦርነት ፣ በፍጅት ፡ ዐልቀዋል ፤ *"አደገች ! … ለማች ! … በለጸገች ! …"* ፡ እየተባለ ፡ በሐሰት ፡ የሚለፈፍባት ፡ **ኢትዮጵያ ፡ በዋጋ ፡ ንረት ፡ ተበልታ ፣ በሙስና ፡ ጐስቍላ ፣ በውንብድና ፡ አንሳ ፥ ጥንት ፡ የጥቍር ፡ ሕዝብ ፡ ኵራት ፡ እንዳልነበረች ፥ ዛሬ ፡ መሣቀቂያቸው ፡ ኾናለች ።**

ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራንም ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ከእናት ፡ ሀገሯ ፡ ገንጥለዋት ፥ የማንም ፡ መንደር ፡ ገነን ፡ መጫወቻ ፡ ኾናለች ። ነዋሪዎቿ ፡ ለስደት ፣ ወደቦቿ ፡ ለምልክዮሽ ፡ የጦር ፡ ሰፈርነት ፡ አለዚያም ፡ ለምዝባሬ ፣ ማዕድኖቿም ፡ ለምልክዮሽ ፡ ነጠቃ ፡ እና ፡ ብዝበዛ ፡ ተዳርገዋል ። **የመንደር ፡ ገነን ፡ ኢሳይያስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ዐይነተኛው ፡ ተልእኮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የባሕር ፡ በር ፡ ጠርንቆ ፡ መዝጋት ፡ እና ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ ፡ ኀይሎችን ፡ እያስታጠቁ ፡ ማስሰምራት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ "ጕልት" ፡ ኾና ፡ በተሰጠችው ፡ በክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራ ፡ ላይ ፡ የሚፈጽማቸውን ፡ የአውሮፓን ፡ "ፌዎዳሊዝም" ፡ የሚያስታውሱ ፡ ውንብድናዎች ፡ ኹሉ ፥ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ አይተው ፡ እንዳላዩ ፣ ሰምተው ፡ እንዳልሰሙ ፡ እየኾኑለት ፥ ፀረ-ኢትዮጵያ ፡ ተልእኮውን ፡ እስከፈጸመላቸው ፡ ድረስ ፡ አሞላቅቀው ፡ ይዘውታል ።**

በቀረችው ፡ ኢትዮጵያ ፥ ከደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ የተነቀለ ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ዐረምን ፡ ምልክዮሽ ፡ ዘርቶባት ፥ ህልውናዋን ፡ ፈትኖባታል ። ነገር ፡ ግን ፥ ሥር ፡ መሠረቷ ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፣ እጅግ ፡ ረቂቅ ፡ በመኾኑ ፥ ይህ ፡ ለምልክዮሽ ፡ አልተገኘለትም ። የጭፍን ፡ ጥቃቶቹ ፡ ጐዷት ፡ እንጂ ፡ አላጠፏትም ። **ይልቁንም ፥ ዛሬ ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሀገራዊ ፡ ሕዝብናው ፡ ወይም ፡ በዐምሐራነቱ ፡ የፋኖነት ፡ ትግሉን ፡ ከወጠነ ፡ ወዲህ ፥ ኢትዮጵያ ፡ ነፍስ ፡ ዘርታለች ፥ የድኅነት ፡ መንፈስ ፡ ቀርቧታል ፤ ኢትዮጵያ ፡ አፋርሳለች ! መጪው ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ፈታኝ ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዕለት ፡ ወደ ፡ ዕለት ፡ ሸክሙም ፡ እየቀለለላት ፥ ዐቅሟም ፡ እየሞላላት ፥ ጠላቶቿም ፡ ውቃቢ ፡ እየራቃቸው ፥ ወደ ፡ ሙሉ ፡ ህልውናዋ ፡ ትሸጋገራለች ።**

ባንጻሩ ፥ **ላለፉት ፡ 33 ፡ ዓመታት ፡ ምልክዮሽ ፡ በጥንቃቄ ፡ ሲኰተኰታቸው ፡ የኖሩት ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ እና ፡ የሻዕቢያ ፡ የውንብድና ፡ ይዞቶች ፥ ዐፈር ፡ እንደ ፡ ከዳው ፡ ዛፍ ፡ ደርቀው ፥ በግንቦት ፡ እንደ ፡ ተቈረጠ ፡ ዕንጨት ፡ ጠንጥነው ፡ ሊገረሰሱ ፡ ተቃርበዋል ።**

ባንድ ፡ ወገን ፥ ዙሪያዋን ፡ የለየለት ፡ ጦርነት ፡ እየተካኼደ ፡ *"ዐዲስ ፡ አበባን ፡ አስዋብኩ ፡ …"* ፡ እያሉ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ሥሉጥ ፡ ሕዝብ ፡ በከረሜላ ፡ እንደሚያባብሉት ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ለመደለል ፡ መብከንከን ፤ በሌላው ፡ ወገን ፥ የእነመንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፦ *"32 ፡ ቢልዮን ፡ ዛፍ ፡ ተክልኹ ፣ …"* ፡ እያሉ ፡ መበጥረቅ ፥ "ከወደቁ ፡ ወዲያ ፡ መፈራገጥ"ን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ኾኗል ። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፡ የመጨረሻው ፡ መጨረሻ ፡ ተቃርቧል ፤ መጨረሻው ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ሰላማዊ ፡ እንዲኾን ፥ ስለ ፡ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እና ፡ ስለ ፡ አንድያ ፡ ሕዝቧ ፡ ፍቅር ፡ ስንል ፥ ሌት ፡ ተቀን ፡ እንጨነቃለን ፣ እንጠበባለን ፤ **ከመንደር ፡ ገነን ፣ ከከሃዲ ፡ እና ፡ ከዐራጅ ፡ ጋራ ፡ ግን ፡ ድርድር ፡ ፈጽሞ ፡ አይታሰብም ።** ሰላማዊው ፡ መንገድ ፡ የማይገኝ ፡ ቢኾን ፡ ግን ፥ የሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡ ኹሉ ፡ ተከፍሎ ፥ **የኢትዮጵያንና ፡ የአንድያ ፡ ሕዝቧን ፡ እግዚእና ፡ እናስከብራለን ፥ የሀገር ፡ ከሃዲዎችንም ፡ ለፍርድ ፡ እናቀርባለን ።**

በዚህ ፡ መኻከል ፡ ምልክዮሽ ፡ አለ ። ምልክዮሽ ፥ መልኩን ፡ ይለዋውጣል ፡ እንጂ ፡ አይሞትምና ፥ አኹን ፡ ላይ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ለዘለዓለም ፡ ወደሚያሰናብትበት ፡ የመጨረሻ ፡ ረድፉ ፡ ተሸጋግሯል ። ይህ ፡ የመጨረሻ ፡ ረድፍ ፡ ሦስት ፡ ቀድመው ፡ መናድ ፡ ያለባቸውን ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ የቆመችባቸውን ፡ ዐምዶች ፡ ለይቷል ፦

- አንደኛው ፡ ዐምድ ፡ የአጋቦስ ፡ ወሰሎሞናዊው ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት ፡ እና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዘውድ ፡ ሥርዐት ፡ ነበር ፥ ርሱን ፡ በቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፈጻሜ ፡ መንግሥትነት ፡ "ፈጽሜዋለኹ" ፡ ብሎ ፡ አምኗል ፤ ጣልያንም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ …
- ኹለተኛው ፡ ዐምድ ፡ የዐምሐራ ፡ ሀገራዊነት ፣ የዐምሐራ ፡ ኢትዮጵያዊነት ፣ የዐምሐራ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብነት ፡ ነው ፤ ይህ ፡ የማይታለፍ ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾኖበታል ፥ በፋኖ ፡ ዐርበኝነት ፡ የዐምሐራን ፡ አይቈረጠሜነት ፡ አግኝቶታል ። *"ገንዘብ ፡ ካለ ፥ በሰማይ ፡ መንገድ ፡ አለ"* ፡ በማለት ፡ ይመስላል ፥


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

ምልክዮሽ ፡ በገንዘብ ፡ የመለመላቸውንና ፡ ያደራጃቸውን ፡ ምንደኞቹን ፡ አስሰማርቶ ፥ ዐምሐራ ፡ የመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የግብር ፡ ስሙ ፡ መኾኑ ፡ እየታወቀ ፥ አለማቋረጥ ፦ "ዐማራ ፡ ጎሳ ፡ ነው ! ዐማራ ፡ ከፊል ፡ ሕዝብ ፡ ነው ! ዐማራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ 'ሴማዊው' ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፤ ሌሎቹ ፡ ኵሻውያን ፡ ናቸው ! የዐማራን ፡ ማኀበረሰብ ፡ ከኢትዮጵያዊነት ፡ ለይተን ፡ እናደራጃለን" ፡ እያሠኘ ፡ የውሸት ፡ እና ፡ የቅዠት ፡ ስብከቱን ፡ በመንዛት ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ "ዐምሐራ ፡ በኾነ" ፡ እና ፡ "ዐምሐራ ፡ ባልኾነ" ፡ በኹለት ፡ ወገኖች ፡ ሊከፍለው ፡ ይመኛል ። "ዐማራ ፡ በክልሉ ፡ ነጻነቱን ፡ ያውጅ !" ፣ "የዐማራ ፡ መሬቶች ፡ ይመለሱለት !" ፡ እያለም ፥ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ ለኹለት ፡ ለመክፈል ፡ ይቃጣል ። ይህን ፡ የውሸት ፡ ስብከቱን ፡ ለማጽናትም ፡ የንጹሓንን ፡ ደም ፡ በገፍ ፡ እያስፈሰሰ ፥ "ዐማራ ፡ 'በዘሩ' ፡ ምክንያት ፡ ተገደለ ! በዐማራ ፡ 'ዘርነት' ፡ እስካልተደራጃችኹ ፡ ግድያው ፡ ይቀጥላል !" እያሠኘ ፥ ከበደል ፡ ኹሉ ፡ የከፋውን ፡ በደል ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ይፈጽማል ፥ ያስፈጽማል ።

- ሦስተኛው ፡ ዐምድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፥ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ትግሉን ፡ ተያይዞታል ፤ ... ፡ አይ ፡ አለማወቅ ! ከእግዚአብሔር ፡ መታገሉን ፡ አላወቀውም ፡ ... ።

ይህ ፡ ኹሉ ፡ በእልክ ፡ የሚፈጸም ፡ "የክዳት ፡ ፖለቲካ" ፡ መጨረሻው ፡ ጥፋት ፡ ስለ ፡ መኾኑ ፡ አንድ ፡ እና ፡ ኹለት ፡ የለውም ።

መደምደሚያውን ፥ ኢትዮጵያን ፡ ሊገድላት ፡ እንደማይችል ፡ ልቡ ፡ ባወቀ ፥ ምልክዮሽ ፥ በባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴዎቹ ፡ አንደበት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ማንኳጠጥን ፡ መርጧል ፤ ይህም ፡ መሸነፉን ፡ በአማን ፡ መስክሮበታል ። በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ኹሉን ፡ ዐይነት ፡ ተንኰልና ፡ ክፋት ፡ ሲያፈራርቅ ፡ ኖሮ ፥ መጨረሻውን ፡ እንሆ ፡ ዐመደ ፡ ዐፋሽ ፡ ኾነ ፤ ብልኀት ፡ እንዳለቀበት ፡ በይፋ ፡ ታየ ፥ በተረዳ ፡ ታወቀ ።

ከእንግዲህ ፥ የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ መንግሥትም ፡ ኾነ ፡ ሌላ ፡ ግብር ፡ ዐበር ፡ መንግሥት ፥ በኢትዮጵያ ፡ የውስጥ ፡ ጕዳይ ፡ ገብተው ፡ ዳግመኛ ፡ ለማሸማገልም ፡ ኾነ ፡ ለማጥፋት ፡ አይፈቀድላቸውም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዐውቋቸዋል ፤ ዳግመኛ ፡ አይታለልላቸውም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ ጠላቶችኽን ፡ አሳፍረኻቸዋል ፤ ሤራቸውንም ፡ አክሽፈኸዋል ። "ከፋፈልነው !" ፡ ሲሉኽ ፡ አንድ ፡ ኾነኽ ፡ ተገኝተኻል ፤ "አጠፋነው !" ፡ ሲሉኽም ፥ ለህልውናኽ ፡ የምትጋደል ፡ አንበሳ ፡ ኾነኽባቸዋል ። **ከኹሉም ፡ በላይ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ካራ ፡ ሲስሉብኽ ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፥ ወይ ፡ ራሳቸው ፡ በካራ ፡ ተበልተዋል ፣ ወይ ፡ ከካራ ፡ ኹሉ ፡ የባሰ ፡ ካራ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ተመዞባቸው ፡ ከሞት ፡ ጋራ ፡ ተፋጠው ፡ እፈተና ፡ ውስጥ ፡ ገብተዋል ።**

**ከእንግዲህ ፡ የሚቀርኽ ፥ ትግልኽን ፡ በመላ ፡ ሀገርኽ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድል ፡ በመቀጠል ፥ በሦስት ፡ ረድፎች ፡ የተከፈለውን ፡ አንድያ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማኽን ፡ መፈጸም ፡ ብቻ ፡ ነው ፦**

- **ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ ማስከበር ፤**
- **ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ መሥራት ፤**
- **ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥትኽን ፡ መመሥረት ።**

**በሀገራዊ ፡ እግዚእና ፡ ጕዳይ ፡ ከማንም ፡ ጋራ ፡ ድርድር ፡ አይኖርም ፤** የድርድሩ ፡ ዘመን ፡ ዐልፏል ። የኢ..ፌ..ዴ..ሪ. ፡ እና ፡ የሻዕቢያ ፡ መንደር ፡ ገነኖች ፡ እና ፡ በደለኞች ፡ ጭፍሮቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ተይዘው ፡ እና ፡ ለሹም ፡ ተላልፈው ፥ በሕዝብ ፡ አደባባይ ፡ ለፍርድ ፡ ይቀርባሉ ።

**ምልክዮሽን ፡ ማንም ፡ ድል ፡ አያደርገውም ፤ የራሱ ፡ ምግባር ፡ ድል ፡ ለመኾን ፡ ይዳርገዋል ፥ ከዚህም ፡ ፍጻሜው ፡ ሊያድነው ፡ የሚችል ፡ ምድራዊ ፡ ኀይል ፡ አይኖርም ❖**

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ..ህ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።